ልጆች // አበባዎች

ልጆች // ተስፋዎች

ልጆች // ደስታዎች

ልጆች// ፍቅሮች ናቸው

....

**ልጆች እናንተ ፍቅር ናችሁ እና ለሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ፍቅርን ሳትሳሱ መግቡ እሺ~**

**ጣ ፋ ጭ**

*******

# ተመስገን።

**ልብ-ወለድ**

ተመስገን የሚባል አንድ ልጅ ነበረ።
ተመስገን ለወላጆቹ አንድ ብቸኛ ልጃቸው ነው።
ተመስገን የተወለደው ይልማና እና ዴንሳ ነው።
ይልማና እና ዴንሳ የሚገኘው በጎጃም ክፍለሀገር ነው ።
የተመስገን ወላጆች በይልማና እና ዴንሳ ነዋሪዎች ዘንድ
እጅግ የተመሰገኑ፣ የተከበሩ እና የሚወደዱ ናቸው።
የተመስገን ወላጆች እግዚአብሔርን በጣም የሚወዱ እና የሚያከብሩ
በመሆናቸው በኑሮዋቸው ዝቀተኛ ወገኖችን የሚረዱ በችግራቸውም
ደራሽ የሆኑ ናቸው።

የተመስገን ወላጆች በጣም ለረጅም ጊዜ ልጅ ሳይኖራቸው
ቆይቶ እግዚአብሔርን አጥብቀው ለምነው ነበር ተመስገን የሰጣቸው።
ተመስገን ያሉትም ልጅ የሰጣቸውን ፈጣሪ አምላካቸውን ዘወትር ልጃቸውን
በጠሩ ቁጥር ለማመስገን እንዲረዳቸው ፈልገው ነው።

ተመስገንም ከተወለደበት ዕለት ጀምሮ በጣም የተመሰገነ የተወደደ ልጅ
ሆነላቸው።

ተመስገን ለትምህርት ሲደርስ ወላጆቹ በአቅራቢያቸው በሚገኘው የቄስ ትምሕርት ቤት አስገቡት። ተመስገን እጅግ የተለዬ ጸጋ ስለ ነበረው ጊዜ ሳይወስድበት ነበር ፊደልን የቆጠረው። ከዛም በመቀጠል አቡጊዳን መልእክተ ዮሐንስን ስድስት ወር ሳይሞላው አጠናቀቀ።

... ልጆች የተመሰገን ክፍል ሁለት ታሪክ ይቀጥላል ...

# የተሰፋ በር .... ለወላጆች

ውርሰ ኢትዮጵያ
***

*ከሥርጉተ ሥላሴ*
*ጥር 2003 ዓ.ም.*

ጤና ይስጥልኝ ወላጆች እንደ ምን አላችሁ? ደህና ናችሁ ወይ? ... ኑሮ እንዴት ይዟችኋል?
እኛም ደህና ነን። ከዚህ ስደት ከሚሉት ጋር ይህው እንታገላለን። ለመሆኑ ወላጆች ክረምቱ በገባባት አካባቢ የምትኖሩ የዘንድሮ ቅዝቃዜ የሚቻል ይመስላችኋልን? በጣም ይበርዳል አይደል ...?

ወላጆች የዛሬ እርአሰ ጉዳያችን ለልጆች ትምሕርተ ዜግነትን በቤት ውስጥ ለማስተማር አቅዶ መፈጸም ለይደር ሊቀጠር አይገባም የሚል ይሆናል። እርግጥ እርእሰ ጉዳዩ ሰፊ በመሆኑ በተከታታይ የተወሰኑ ነጥቦችን ለማንሳት እሞክራለሁ።

ወላጆች የዜግነት ጉዳይ የራስነት፣ የእኔነት፣ የማንነት፣ የውስጥነት መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የእኛነታች መታወቂያ ካርዳችን ዜግነታችን ነው። ምልክታችን ዜግነታችን ነው። አሻራችን ዜግነታችን ነው። መለዮአችንም ዜግነታችን ነው።

ስለዚህ የወላጆች የመጀመሪያ የተግባር መነሻቸው ሊሆን የሚገባው ጉዳይ ወላጆች ለልጆቻቸው የዜግነታቸውን ጉዳይ መንገር ማስተማር ነው። የዜግነታቸው ሚስጢር ከሰውነታችው ጋር አብሮ ያድግ ዘንድ፣ ደማቸውን በዜግነት ቅመም መፍጠር ያስፈልጋል። ዜግነታቸው ወይንም ኢትዮጵያዊነታቸው በደማቸው ወስጥ በፍጹም ሁኔታ እንዲዘዋወር እና የደስታቸውም ምንጭም እንዲሆን የማድረግ የወላጆች መቅድም ግዴታ ሊሆን ይገባል።

እርግጥ ነው ወላጆች መጀመረያ ነገር እራሳቸውም ቢሆኑ በዚህ ሚስጢረ ነገር መቃኘት ይገባቸዋል። ከምንም እና ከማንም በላይ ... ማለትም ከፈጣሪያቸው በታች ቀጥሎ ያለው ዕንቁ ጉዳይ ኢትዮጵያዊነታቸው ስለ መሆኑ ወላጆች እራሳቸው ክህነቱ ሊኖራቸው ይገባል።

... እራሳቸው ያመኑበትን ወይንም የተለወጡበት ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ህይወታቸው እራሱ ለልጆች ትምሕርት ቤት እንዲሆን ማደረግ በቀላሉ የሚቻል ይመስለኛል። አብሶ በዚህ ዘመን ... ስለ አንዲት ቅድስት ሀገር ማሰብ፣ ጸጋው የተሰጣቸው ብቻ የሚመገቡት ሚስጢር ይመስለኛል። ጌጣችን፣ ውበታችን፣ ማማራችን መሰረቱ አንድነታችን ነው እና!

ወላጆች ለልጆች ሊነገሯቸው ሊያወርሷቸው የሚገባው መሰራታዊ ጉዳይ የኢትዮጵያዊነታችው ሰላማዊ ጉዳይ ብቻ መሆን አለበት .... ይቀጥላል ...